

፨45-1፨

# ጠቃሚ ምክር
# "ክርስትያን መሆን ከበደኝ" ለሚሉ

አንድ ክርስትያን ነጋዴ አንድ ጊዜ ምርር ብሎት "አሁንስ ፈጽሞ ተስፋ ቆረጥኩ፤ የክርስትናን ሕይወት መተው አለብኝ፤ ምክንያቱም በንግድ ዓለም ውስጥ ሳይጭበረብሩ፥ በሀቅና በእውነት ነግዶ ማትረፍ ፈጽሞ አይቻልም። ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ተንኮለኞች፥ በጭካኔ የተሞሉና ሁለት ምላስ ያላቸው ናቸው። አንድ ሰው ይህንን በሚመስል ሕብረተሰብ መካከል ለመኖር ሕሊናውን ማደንዘዝ፥ እውነት ላልሆነውም ነገር ጥርሱን ነክሶ መቆም ይኖርበታል። አሸንፎ ለመኖር በመንገዱ ወይም በፊቱ የሚቆሙትን ሁሉ እየረጋገጠ ማለፍ አለበት። ስለዚህ ጥሩ ክርስትያን ሆኖ መኖር በጣም ያስቸግራል" አለ። ይህ ክርስትያን ነጋዴ የረሳው ነገር ቢኖር በማጭበርበር የሚገኘው ሀብት ዘላቂ የሆነ ደስታ ሊሰጠው የማይችል መሆኑን ነው። *"በግፍ ባገኘው ሀብት ቤቱን ለሚሠራ፣ በእምነት አጉዳይነትም በቤቱ ላይ ፎቅ ለሚጨምርበት፣ የገዛ አገሩን ሰዎች ያለ ዋጋ ለሚያሠራና ያለደመወዝ ጉልበታቸው ለሚበዘብዝ ወዮለት!"* ይላል ኤርምያስ 22፥13።
ይህንን ዓይነት የተስፋ መቁረጥ ድምጽ የሚያሰሙት ብዙዎች ናቸው፥ ሥጋውን መቆጣጠር ያቃተው ወጣት "በወጣትነት ይህን ዓይነት ትኩስ ዕድሜ ይዞ ዓለማችን በርኩሰቷ ከሰዶምና ከገሞራ በባሰችበት ዘመን፥ የጾጢፈር ሚስት ዓይነቶቹ በበዙበት ዓለም፥ ሥጋን አሸንፎ በቅድስና መኖር የማይቻል ነው፤ የክርስትና ሕይወት ምናልባት ለእንደኔ ዓይነቱ አይሆንም ይሆናል" በማለት የተስፋ መቁረጥ ንግግር ያሰማል። ዓለምንና በውስጧ ያለውን ሙሉ በሙሉ ያልተወው ደግሞ በሁለት ዓይነት ሕይወት ውስጥ ስለሚኖር በክርስትና ሕይወት ውስጥ ያለው ግፊትና ትግል ይህን ያህል አይሰማውም። ስለዚህ ለእርሱ ክርስትያን መሆን ቀላል ነው።

## ክርስትና አቋሙ እየላላ መጥቶ ይሆን?

ጥንት በክርስትና ምክንያት ብዙዎች ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል። ክርስትያን መሆን ስደትን፣ መጠላትን፣ የከፋ እንደሆነም ሞትን የሚያስከትል መሆኑ ስለሚታወቅ የሚቀበለው በጣም የተወሰነ ነበር (መዝሙር 123፥4)። አሁንስ ክርስትና የሚያስከፍለው ዋጋ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ብዙዎች ይረባረቡበት ይሆን? በአሜሪካ የክርስትና አቋም ባለፉት አሥራ ስምንት ዓመት ውስጥ እንኳን ብዙ ለውጦችን አሳይቷል።
"በዋተርጌቱ ቅሌት" ምክንያት ወህኒ ቤት ገብቶ የነበረው የፕሬዜዳንት ኒክሰን የቅርብ አማካሪ የነበረው ቻርለስ ኮልሰን እሥራቱን ጨርሶ ሲወጣ "እንደገና መወለድ" (born Again) የሚለው መጽሐፉን አሳተም። በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ጌታን እንዴት እንዳገኘና "የዋተር ጌቱን ቅሌት" ልምምድ ጽፎ ነበር። በዚህ መጽሐፍ ምክንያት ብዙዎች ስለ ክርስትና እምነት ያላቸው አስተየየ ተለወጠ።

- በ1976 ጌታን እንደ ግል መድኃኒቱ ያወቀው ጂሚ ካርተር የአሜሪካ ፕሬዜዳንት ሆኖ ሲመረጥ ክርስትና በሕብረተስቡ ዘንድ እንደመጥፎ ነገር መታየቱ እየቀረ መጣ።
- በ1986 ዓ.ም. በተደረገው ጥናት ሰላሳ ሁለት ከመቶ (32% የሚሆኑት አሜሪካውያን ራሳቸውን "እንደገና የተወለዱ ክርስትያኖች" (Born Again Christians) ብለው እንደሚጠሩ ታወቀ።
- እንዲሁም በዚሁ ዓ.ም. የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው ሃምሳ ሰባት ከመቶ (57%) የሚሆኑት አሜሪካውያን "ሃይማኖት ለዘመኑ ችግር መፍትሄ ይሰጣል" ብለው ያምኑ ነበር።

ለብዙ ዘመናት ኢትዮጵያ በሃይማኖተኛነቷ የታወቀች አገር ናት። ይሁን እንጂ በሯ ለወንጌል ፍጹም ዝግ ነበር። በድፍረትና በቆራጥነት ወንጌልን ለመስበክ በመጡት ሚስዮናውያን ላይ ከፍተኛ የስደት በትሯን ዘርግታለች። ወንጌልን ከሚሲዮናውያን ላይ በተቀበሉት ኢትዮጵያውያን ላይም ብዙ ስደትና መከራ ደርሶባቸዋል። "ጴረ ማርያም" የሚል ቅጽል ስም በመስጠት በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ተደርገዋል። እኔም ወንጌልን ከሚሲዮናውያን ከተቀበሉት መካከል አንዱ ነኝ። በዚያን ጊዜ ጌታን የምናውቀው ቁጥራችን በጣም ትንሽ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ልጆችና ወጣቶች ብቻ ነበርን። በአሁኑ ጊዜ ግን ወደ ቤተ ክርስትያን የሚጎርፉት ጌታን እንደ ግል መድኃኒታቸው አድርገው የሚቀበሉት ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ አዛውንትም ጭምር ናቸው። ብዙዎች ለክርስትና ልባቸው ይህን ያህል

ክፍት ከሆነ ታዲያ ጥሩ የክርስትና ሕይወት አኗኗር የማይታይባቸው ለምን ይሆን? ወይንም የክርስትና ባህሪ በዕለታዊ ሕይወታቸውና ኑሮአቸው ላይ በደንብ የማያንጸባርቀው ለምንድነው? ክርስትናስ የሚያስከፍለው ዋጋ ዝቅ ብሎ ይሆን? ይህንን ለመረዳት ሁለቱን የክርስትና ዓይነቶችን ማወቅ ይጠቅማል።

ሀ. ባህላዊ ክርስትና

ባህላዊ ክርስትያኖች እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ በመቀበል ፈንታ ሌላ እነርሱ የሚመርጡትን ዓይነት እግዚአብሔር እንዲሆን የሚፍልጉ፥ ቃሉን በሥራ ላይ የማያውሉ ናቸው (ያዕቆብ 1፥22-25)። ጠባብ በሆነው አመለካከታቸው እግዚአብሔርን የሚያዩት የሚጠይቁትን ሁሉ በመስጠት የልጅ ልጆቹን እንደሚያበላሸው አያት ነው። ባህላዊ ክርስትና የሕብረትሰቡን አስተሳሰብና የአሠራር አቋም ለመለወጥ ያልቻለ፣ ኃይሉን ያጣ ሃይማኖት ነው። በዚህ ዓይነቱ ክርስትና ውስጥ ያሉ በእግዚአብሔር አስተሳሰብ ውስጥ ራሳቸውን ማኖር ሲገባቸው እግዚአብሔር በእነርሱ አስተሳሰብ ውስጥ እንዲሆን ይፈልጋሉ። እንደነዚህ ላሉት የክርስትና ሕይወት ይህን ያህል ከባድ አይደለም። እንደልባቸው ተዝናንተው ይኖራሉ፤ የሚከፍሉትም ዋጋ የለም።

ለ. እንደ እግዚአብሔር ቃል የተመሠረተ ክርስትና

በዚህ ዓይነቱ ክርስትና ውስጥ ያሉት በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በራሳቸው አስተሳሰብ ወይንም መሪ ሀሳብ አይመሩም። በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ስለሆኑ በሰላም የተሞላና አሸናፊ የሆነ ሕይወት ይለማመዳሉ። ለደህንነታቸው የሚታመኑት በክርስቶስ ብቻ ነው። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለሚሰጣቸው የሕይወት መመሪያ ታዛዦች ናቸው። በሌላ በኩል መረዳት ያለብን የሚያድነን እምነታችን እንጂ ታዛዥነታችን እንዳልሆነ ነው (ሮሜ 1፥5)። ስለዚህ ነው ባህላዊ ክርስትና ውስጥ ያሉት እምነት እያላቸው ባለመታዘዝ ሕይወት ውስጥ የሚመላለሱት። እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ሕይወታቸውን ለሚመሩት፥ ለእነርሱ ክርስትና ዋጋ ያስከፍላቸዋል። በዚህም ደስ እንዲላቸው የእግዚአብሔር ቃል ይነግራቸዋል (1ኛ ጴጥሮስ 4፥16)። "የክርስትና ሕይወት ከበደኝ" ቢሉ ይህን ያህል አይገርመንም።

## ክርስትና ሕይወት የማይከብዳቸው እንዴት ዓይነቶቹ ናቸው?

ማልኮለም መግሪጅ እንቁራሪትን በሙቅ ውሃ ውስጥ መቀቀል እንዴት እንደሚቻል ሲያስረዳ፥ "እንቁራሪቷን ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ከትቶ ቀስ በቀስ የሙቀቱን ኃይል መጨመር ነው። እንቁራሪቷ የሚሆነው ሳታውቅ ቀስ በቀስ በፈላ ውሃ ውስጥ ተቀቅላ ትሞታለች" አለ። ሰይጣንም ክርስትያኖችን ወዲያው የሞቀ ዓለም ውስጥ አይከትም። ይህ ቢሆን ክርስትያን ተፈናጥሮ ይወጣ ነበር። በዚህ ምትክ ግን ቀስ በቀስ ልባቸውን እየሳበና እያታለለ ይወስዳል። ለዘብ ያለ የክርስትና ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ የሕይወት ፍልስፍናቸውና እንዲሁም የሥነ ምግባር አቅማቸው ይህን ያህል በዓለም ውስጥ ካለው ሰው የተለየ አይደለም። በዓለም የተበረዘ ሕይወት የሚኖሩትን ክርስትያኖች ኢየሱስ እንዲህ ይላቸዋል። "*ሥራህን አውቃለሁ፤ በራድ ወይንም ትኩስ ብትሆንማ መልካም በሆነ ነበር፤ በራድ ወይንም ትኩስ ሳትሆን ለብ ያልህ ስለሆንህ ከአፌ አውጥቼ ልተፋህ ነው። እኔ ሀብታም ነኝ ብዙ ሀብት አለኝ የሚጎድለኝ ምንም የለም ትላለህ፤ ነገር ግን ጎስቋላ ምስኪን ድሃ፣ ዕውር የተራቆትህም መሆንህን አታውቅም*" (ራዕይ 3፥15-17)። ለብ ያለ ክርስትያን እንደ ዕንቁራሪቷ ቀስ በቀስ በፈላ ውሃ በመቀቀል ላይ ያለ የኃጢአት ሕይወት መኖርን የተለማመደና ህሊናው የሞተ በመሆኑ "ክርስትና ከበደኝ" ብሎ ለእርዳታ አይጮህም።

## ክርስትና አክብደው ወይንም አቅልለው ከሚያሳዩ የስህተት ትምህርቶች እንጠንቀቅ

የክርስትና ሕይወት የትግል ሕይወት ነው። መንገዳችን የጽጌረዳ አበባ ምንጣፍ የተነጠፈበት አይደለም። እንዲያውም ሸካራ ነው። አንዳንድ ሰዎች የክርስትናን ሕይወት የሌለውን ዓይነት መልክና ቅርጽ ሊሰጡት ሲሞክሩ ይታያሉ። አሳምረውና ቀባብተው ስለሚያቀርቡት የብዙዎችን ልብ መማረክ ችለዋል። ስለ ክርስትና ሕይወትና ዕድገት ከሚያስተምሩት የተሳሳተ ትምህርት መካከል ጥቂቱን ለመጥቀስ እንሞክራለን።

ሀ. "ክርስትያንት ስንሆን ችግራችን ሁሉ ይቃለላል"

*መጽሐፍ ቅዱስ የክርስትና ሕይወት ችግር የሌለበት ነው ብሎ ተስፋ አይገባልንም። ጌታን እንደ ግል መድኃኒታችን ስንቀበለው እርግጥ ነው አስተማማኝ ሰማያዊ ቤት እንደሚኖረን ያረጋግጥልናል። ይሁን እንጂ ምንም ዓይነት ችግርና መከራ አታዩም ብሎ ቃል አልገባልንም። እንዲያውም በክርስትና ሕይወታችን በገፋን ቁጥር ጉዞአችን ከባድና ፈተና የበዛበት ይሆናል። ጴጥሮስ የእምነታችን እውነተኛነት እንደሚፈተን ይነግረናል። "ይህ ፈተና የደረሰባችሁ የእምነታችሁን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ነው፤ የሚጠፋ ወርቅ እንኳ በእሳት ይፈተናል፤ ከወርቅ ይልቅ የከበረ እምነታችሁ እንደዚሁ መፈተን አለበት" ይላል* (1ኛ ጴጥሮስ 1፥7)።

ለ. “ለችግሮቻችን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ መልስ ይሰጠናል”

መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወታችን ለሚያጋጥመን ችግርና ጥያቄ ለሚሆንብን ለብዙው መልስ አለው። ለሁሉም ግን መልስ አይሰጠንም። ለሁሉም መልስ ማግኘት ቢቻል ኖሮ ኢዮብ መልስ ባገኘ ነበር። ስለሆነም አልፎ አልፎ በእምነት መራመድ የምንገደድበት ጊዜ ይኖራል። እንዳስፈላጊነቱ የሚቀጥለው እርምጃችን ምን መሆን እንዳለበት እንዲያሳየን በጌታችን መታመን የሚይስፈልግን ጊዜ አለ።

ሐ. “ችግር የሚገጥመን ጥሩ ክርስትያን ባንሆን ነው”

ችግር የሚያገጥመን ሥጋ ለባሽ ሰዎች በመሆናችን እንጂ ጥሩ ክርስትያኖች ስላልሆንን አይደለም። ክርስትያን ሁሉ ከችግር ነጻ አይደለም። ሁላችንም የራሳችን ችግር አለብን። በችግር ውስጥ የምናልፈው ደካማ የሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ስለምንኖር አይደለም ወይንም ችግር ከሌለብን ደግሞ ከሌሎች የተሻለ ጥሩ የክርስትና ሕይወት በመኖራችን አይደለም። እንዲያውም ታላላቅ መንፈሳዊ አባቶች ታሪካቸውን ስናጠና አብዛኞዎቹ በብዙ ትግልና መከራ ውስጥ ያለፉ እንደነበሩ እናያለን። ኢዮብ በብዙ መከራ ውስጥ አልፎአል፤ ይሁን እንጂ ለጥይቄው ማለትም ለምን በመከራ ውስጥ ማለፍ እንዳለበት ከእግዚአብሔር መልስን አላገኘም። ኢዮብ በመከራና በፈተና ውስጥ ማለፍ የቻለው ኃጢአተኛ ስለሆነ አልነበረም። ይህ ቢሆን ኖር ቅድስናውን እግዚአብሔር ራሱ አይመሰክርለትም ነበር (ኢዮብ 1፥8)።

መ. “ቃሉን መጠቀም ስንችል ችግራችን ይጠፋል”

የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ለችግራችን መፍትሄ ወዲያው ይሰጣል ብሎ ማመን ትልቅ ስህተት ነው። መጽሀፍ ቅዱስ መመሪያ ካርታ (Map) ነው። ካርታ አቅጣጫችንን ያመለክተናል እንጂ ከፈለግነው ሥፍራ አያደርሰንም። ከፈለግነው ቦታ ለመድረስ የራሳችንን ድርሻ ማድረግን ይጠይቃል። የእግዚአብሔር ቃል አስተማማኝ የሆነ መመሪያችን ነው። ዳዊት *“ቃልህ እንደ መብራት ይመራኛል፤ ለመንገዬም ብርሃን ነው”* ይላል (መዝሙር 119፥105)። መጽሀፍ ቅዱስ ብርሃን ሆኖ የሚመራን እንጂ የፈለግነውን አጠገባችን ስቦ የሚያቀርብለን የአስማት መጽሀፍ አይደለም።

## የክርስትና ሕይወት ቀላል መንገድ የለውም

ሁላችንም ክርስቶስን መምሰል እንፈልጋለን። እርሱ የነበረውን ዓይነት ንጹህ ሕይወት፣ ፍቅርና ቆራጥነት እንዲኖረን እንመኛለን። በዓለም ውስጥ ያሉትን ተቃዋሚ ኃይሎች በድፍረት መቋቋም፣ በሞት ሸለቆ ውስጥ ሳንዝልና ሳንፈራ መሻገር እንወዳለን። በአጠቃላይ ብርቱዎችና ደፋሮች መሆን እንፈልጋለን። ችግራችን ግን ከላይ የገለጽናቸውን ሁኔታዎች ሆነን ለመገኘት የሚያስከፍለውን ዋጋ መክፈል አንፈልግም። ትዕግሥታችንን በሚያሰጨርስ ኃይለኛ ግፊት ውስጥ ማለፍን አንወድም። ሁላችንም የምንፈልገው ትግል የሌለበት፣ የማያስጨንቅ፣ ቀላል የተመቻቸ ህይወት መኖር ነው። ያዕቆብ ለማጥፋት የሚሞክረው ይህን ዓይነቱን የተሳሳተ እምነትን ነው (ያዕቆብ 1፥1-15)።
ያዕቆብ ክርስቶስን መስሎ ለመኖር ቀላልና አቋራጭ መንገድ የለም ይላል። ስለዚህ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስብን የመጣው ለዕድገታን ነው ብለን በምስጋናና በደስታ መቀበል አለብን። *“ወንድሞቼ ሆይ! ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ በጣም ደስ ይበላችሁ”* ይላል (ያዕቆብ 1፥2)። ያዕቆብ ሁለት ምርጫ ብቻ እንዳለን ያሳየናል። ይኸውም ተዝናንቶና ተመቻችቶ መኖር ወይንም ክርስቶስን መስሎ መኖር ነው። ሁለቱንም በአንድ ላይ መያዝ አይቻልም። ሳንታገል፥ በቀላሉ የተመቻቸ ሕይወት እየኖርን የክርስቶስን ዓይነት መልክና ባህሪ በእኛ ሕይወት እንዲቀረጽ ማደረግ አይቻልም። በክርስቶስ ላይ የምናየውን ዓይነት የሕይወት ውበትና ጸጋ በእኛ ሕይወት ውስጥ እንዲታይ ከፈለግን ሊቀርጸን በሚችል ሕይወት ውስጥ ማለፍ አለብን።

የክርስትያኖች ሁሉ ዓላማ ክርቶስን መምሰል እንጂ ከሌሎች ክርስትያኖች በልጦ ለመታየት አይደለም። ክርቶስን ለመምሰል የሚፈልግ ክርስትያን በሕይወቱ ከፍተኛ ዓላማ እንዳለው ያውቃል። ከፍተኛ ዓላማ ያለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን አንድ ቦታ ቁጭ በማለት ብቻ ካሰበው ዓላማ መድረስ እንደማይችል ያውቃል። የክርስቶስን ፍቅር፣ ድፍረት፣ ክብርና ንጽሑህ ሕይወት ማድነቅ ብቻ ሳይሆን እንደ እርሱ መሆን ይፈልጋል። ከዚያ ደረጃ እንዳይደርስ እንቅፋት የሚሆንበት ደካማ ጎን እንዳለው በደንብ ያውቃል። ክርስቶስን ለመምሰል ያ ደካማ ጎኑ ጉልበትና ብርታት ማግኘት እንዳለበትም ይረዳል። ክርስቶስን እንድንመስል የሚያስችለን ጉልበት በምቾትና በተለሳለሰ ሕይወት ውስጥ በማለፍ ብቻ የሚገኝ እንዳልሆነ በሕይወታችን ኖረን አይተነዋል። በችግር፣ በመከራ፣ በልዩ ልዩ ዓይነት የሕይወት ግፊትና እንዲሁም በተስፋ መቁረጥ ውስጥ የሚገኝ ነው።

## የክርስትና ሕይወት "መተውን" ይጠይቃል

"ለብ" ያለ ሳይሆን እውነተኛ ክርስትያን ሆኖ ለመኖር የመረጠ ሰው ሊያደርጋቸው የሚፈልጋቸው፥ እንዲኖሩት የሚመኛቸው ልዩ ልዩ ነገሮች ክርስቶስን የማያከብሩ ከሆኑ መተው አለበት። ጳውሎስ "*ከዚህ በፊት ጠቃሚዎች ናቸው ብዬ አምንባቸው የነበሩትን ነገሮች ሁሉ ስለክርስቶስ ብዬ ዋጋ እንደሌላቸው ከንቱ ነገሮች አድርጌ እቆጥራቸዋለሁ*" ይላል (ፊሊጵስዩስ 3፥7)። ዋጋ አለው ብሎ የሚያምንበትን ማንኛቸውንም ነገር ክርስቶስን የሚሸፍንበት ከሆነ መተው አለበት። ጌታን ያወቅሁት በልጅነቴ ነው። ኳስ መጫወት፣ መዝለል፣ መሮጥ ኃጢአት መስሎ ይሰማኝ ስለነበረ ያደግሁት ተጨብጬ ነው። የትምህርት ቤት ጓደኞቼ ሲሮጡ፣ ሲዘሉና ኳስ ሲጫወቱ እኔ አንድ ጥግ ይዤ እነርሱን እያየሁ በነበራቸው ነጻነት በጣም እቀና ነበር። የክርስትና ሕይወት እንደ ልጅ ኳስ መጫወትን የማይከለክል መሆኑን ባለማወቄ በዚህ ብቻ የክርስትና ሕይወት ከባድና መስዋዕትን የሚጠይቅ መሆኑ ይሰማኝ ነበር። ኃጢአት ያልነበረው እንደ ኃጢአት ሆኖ ቢሰማኝም በዚያን ወቅት ለራሴ የምሰጠው መልስ "የተሻለውን ለማግኘት ስል ለማድረግ የምወደውን ነገር በመተው መስዋዕት መክፈል አለብኝ" የሚል ነበር።

## የክርስትና ሕይወት በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል

አማኝ በሕይወቱ ሁሉ ነገር እንዳሰበውና እንደተመኘው ቀጥ ብሎ አይሄድለትም። አልፎ አልፎ ሁኔታው ፈጽሞ ልክ የማይመጡለት ጊዜ አለ። ሁሉም ነገር እንደ ዕቅዱ እንዲሄድለት በብርቱ በሞከረ ቁጥር ያልጠበቀውን ዓይነት ውጤት የሚያገጥመው፣ የጠላቱም የሰይጣን ኃይል ፍጹም ኃይለኛ መስሎ የሚሰማው ጊዜ ይኖራል። አንዳንድ ጊዜ ከሥጋ፣ ከዓለምና ከሰይጣን ጋር ያለበት ጦርነትና ግብ ግብ ይከብድበትና ፍጹም ተስፋ ቆርጦ "አሁንስ አቃተኝ! አሁንስ በቃኝ" ብሎ ክርስትናን እርግፍ አድርጎ ለመተው የሚወስንበት ጊዜ አለ። ክርስቶስን መስሎ ለማደግ በዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ ማለፍ የግድ አስፈላጊ ነው። ይህንን ቀደም ሲል፥ ጉዞአችንን ገና ሳንጀምር አውቀነዋል። "የክርስትና ሕይወት መንገዱ ቀላል ነው" ብለው ነገረውን እንደሆነ የነገሩን ሰዎች በጣም ተሳስተዋል። ይህን ለመረዳት የጳውሎስን ሕይወት መመልከቱ ይጠቅማል (2ኛ ቆሮንቶስ 11፥23-29)። እኛ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በውስጡ አልፈን ያየነው፥ ቀላል ሆኖ አላገኘነውም። እንዲያውም ወደ ፊት በገፋን ቁጥር የክርስትና ሕይወት በጣም እየከበደ እንደሚመጣ ስለምናውቅ ገና ከዚህ የከፋ ብዙ የትግል ሕይወት ውስጥ እናልፋለን ብለን እንጠብቃለን።

## ክርስትያን ሆኖ ለመቆም የግል ጥረትን ይጠይቃል

ኢየሱስ በምድር ላይ የነበረውን ዘመን ያሳለፈው በተለሳለሰና ምቾት ባለው ሕይወት ውስጥ አልነበረም። ረሀብን ስለተለማመደ (ማቴዎስ 4፥2) መራብ ምን እንደሆነ ያውቃል፤ ሰዎች አፌዘውበት ስላየ (ማቴዎስ 27፥29-31) ሲያፌዙብን የሚሰማንን ስሜት ያውቃል፤ ምንም እንኳን ተሸንፎ እጁን ያልሰጠ ቢሆንም በተደጋጋሚ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች አጋጥመውት ስላየ ተስፋ መቁረጥ ምን እንደሆነ ያውቃል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለመሰቀል በደረሰበት ወቅት ምንም ዓይነት ኃይል ሊሰብረው የማይችለው ኃይልና ብርታት ነበረው። የጲላጦስና የአይሁድ አለቆች ጦር መንፈሱን ሊሰብረው አልቻለም። ይህን ዓይነቱን ኃይል ሊያገኝ የቻለው ቀላልና ለስላሳ በሆነ መንገድ አልፎ በመምጣቱ አይደለም። ስለዚህ እኔና እናንተ እንደ ኢየሱስ ብርቱዎች ለመሆን ከፈለግን እርሱ ባለፈበት መንገድ ማለፍ አለብን። "*እኔን መከተል የሚፈልግ ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ*" ይላል (ማቴዎስ 16፥24)።

"ኢየሱስ ይህን የመሰለውን ኃይል ያገኘው ከአባቱ ነው" ማለት እንችላለን፤ በአንድ በኩል እውነትም ነው። ነገር ግን እኔና እናንተ "ይሄ አባባል አሸናፊዎች ሆነን ለመኖር የሚያስችለን ኃይል የሚመጣው ከእግዚአብሔር ስለሆነ በእኛ በኩል ምንም የሚያስፈልግ ጥረት አይኖርም" የሚል እምነት ያስከትል ይሆናል ብለን እንፈራለን። በዚሁ ዓይነት አስተሳሰብ አንዳንድ ሰዎች ጠንካራ ሊያደርጉን የሚችሉ ሁኔታዎች መፈጠር አለባቸው ብለን መጨነቅ የለብንም ብለው ያስባሉ። ይህን ዓይነቱ አስተሳሰብ የተሳሳተ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አደገኛም ነው። በተመቻቸ፣ በራስ ወዳድነት፣ በቀላሉ በሚንሸራተትና ደካማ በሆነ መነፈሳዊ ሕይወት እየኖርን ክርስቶስን መስለን የምንኖርበትን ኃይል እግዚአብሔር ሰጥቶን በመንፈሳዊ ዕድገት ውስጥ እናልፋለን ብሎ ማመን ትልቅ ስህተት ነው። ራሳችንን ማታለል ትተን ክርስቶስ ባለፈበት መንገድ እንለፍ። በክርስትና ሕይወታችን አሸናፊ ሕይወት መኖር ባለመቻላችን እግዚአብሔርን ምክንያት ማድረጋችንንና መውቀሳችንን እናቁም። እስከ መስቀሉ ድረስ ለመድረስ የሚያስችለው ኃይልና ጉልበት ለማግኘት ኢየሱስ በፈተናና በችግር ውስጥ ማለፍ ካስፈለገው እኛ ለዕድገታችን ሌላ መንገድ ይኖራል ብለን እንዴት እናስባለን።

..........................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**